# 100 ጥያቄ እና መልስ

# ስለ አላህ ብቸኛ ተመላኪነት እምነት


## ሰብሳቢና አዘጋጅ፡-

ዐብዱ'ል ዐዚዝ ቢን ሙሀመድ አሽ-ሽዕላን


## መቅድም

የተከበሩ ታላቁ ሸይኽ ሷሊህ ቢን ፈውዛን አል-ፈውዛን የዑለማዎች ከፍተኛ ምክር ቤት አባል እና የፈትዋ ቋሚ ኮሚቴ አባል


## ትርጉም፡-

አቡ ዐብዱ'ል ዐዚዝ/ ዩሱፍ አሕመድ

بسم الله الرحمن الرحيم

## መቅድም

ምስጋና በሙሉ ለአላህ ይገባው!!

ከዚህ በኋላ፦

በተሐድሶ መሪው ሸይኽ ሙሐመድ ብን ዐብዲል ወሐብ - ረሒመሁሏህ - የተዘጋጁ፣ "ሶስቱ መሰረቶች" እና "አራቱ መርሆዎች" ያቀፏቸውን መልእክቶች የያዙ፣ ሸይኽ ዐብዱል'ዐዚዝ ብን ሙሐመድ አሽ-ሸዕላን የጻፏቸውን ጥያቄዎችና መልሶቻቸው አንብቢያለሁ:: ይህንን ታላቅ ኪታብ ለማወቅ የሚያግዝ፣ ግንዛቤን የሚያቀርብ ጥሩና ጠቃሚ ስራ ሆኖ አግኝቸዋለሁ:: አላህ በመልካም ዋጋውን ይክፈለው፣ በእውቀቱም ይጥቀመው::

ይህን የጻፈው፦ ሷሊህ ብን ፈውዛን አልፈውዛን

የከፍተኛ ዑለሞች ምክር ቤት አባል

21/3/1440 ዓ.ሒ.

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው። የአላህ ውዳሴና ሰላምታ ደግሞ የነብያቶችና የመልእክተኞች ሁሉ በላጭ በሆኑት ሙሐመድ ላይ ይሁን…

<u>ከዚህ በኋላ፦</u>

እነዚህ ጥያቄዎችና መልሶች፣ የመሰረቶች ሁሉ መሰረት በሆነው አላህን በብቸኝነት ማምለክ፣ የእርሱ ተቃራኒ ከሆነው በአምልኮ ከፍጡር ጋር ማጋራት እንዲሁም ወደርሱ ከሚያደርሱ ነገሮች በማስጠንቀቅ፣ እንዲሁም የአህለሱና ወልጀማዓ እምነቶች ዙሪያ በሚያጠነጥኑ ጉዳዮች ላይ አጠር አድርጌ ያቀረብኩት ነው።

ለአንባቢያን ግንዛቤ ቀላል እንዲሆን ጥረት አድርጊያለሁ።

በእርሷ፣ ሰዎችን እንዲጠቅምበት አላህን እጠይቃለሁ።

ዐብዱል’ ዐዚዝ ቢን ሙሐመድ አሽ-ሸዕላን

በሪያድ የዐዚዝያ ክፍለ ከተማ የጃልያ ት/ቤቶች ክትትልና የዳዕዋና ትምህርት መደጋገፍ ጽህፈት ቤት ሐላፊ

## አላህን በብቸኛነት የማምለክ እምነት

ጥያቄና መልስ

ጥያቄ - 1፦ አላህን በብቸኛነት የማምለክ እምነትን የምንማረው ለምንድን ነው?

መልስ - 1፦ የመሰረቶች ሁሉ መሰረት፣ ጅንንና ሰውን አላህ የፈጠረበት፣ መልእክተኞችን የላከበት፣ መጽሐፎችን ያወረደበት፣ የጀነትና የእሳት ገበያ የተሰናዳበት፣ ሰዎች ሙስሊምና ከሐዲ ተብለው የተለዩበት በመሆኑ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፦

﴿وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنْسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ﴾

‹‹ጅንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።›› (ዛሪያት ፡ 56)

ጥያቄ - 2፦ እምነታችንን የምንይዘው ከየት ነው?

መልስ - 2፦ ከቁርኣን፣ ከሐዲስና በእርሱ ላይ የዚህ ማህበረሰብ ቀደምቶች ከነበሩበት፤

ጥያቄ - 3፦ የሰው ልጅ ቀብር ውስጥ ስለእነርሱ የሚጠየቅበትና ማወቁ በእርሱ ላይ ግዴታ የሆነበት ሶስቱ መሰረቶች እነማን ናቸው?

መልስ - 3፦ ባሪያው ጌታውን፣ እምነቱን እና ነብዩ ሙሐመድን - ዓለይሂሶላቱ ወሰላም - ማወቅ ነው።

ጥያቄ - 4፦ ጌታህ ማን ነው?

መልስ - 4፦ ጌታዬ፣ ያ እኔንም ይሁን ፍጥረቱን ሁሉ በጸጋው የሚንከባከብ የሆነው አሏህ ነው። እርሱ እኔ የማመልከው ነው። ከእርሱ ውጭ የማመልከው የለኝም።

ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፦

﴿الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ﴾

‹‹ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለሆነው።›› (ፋቲሓህ ፡ 2)

ጥያቄ - 5፦ ጌታህን በምን አወቅከው?

መልስ - 5፦ በምልክቶቹና በፍጡሮቹ አወቅኩት። ከምልክቶቹ - ሌሊቱ፣ ቀኑ፣ ፀሃዩ፣ ጨረቃው ይገኙበታል። ከፍጡሮቹ - ሰባቱ ሰማያትና በውስጣቸው የሚገኙ ፍጡሮች፣ ሰባቱ ምድሮችና በውስጣቸው የሚገኙ ፍጡሮች፣ በሁለቱ መካከል የሚገኙ ፍጡሮች ናቸው።

ለዚህ ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

﴿وَمِنْ آيَاتِهِ اللَّيْلُ وَالنَّهَارُ وَالشَّمْسُ وَالْقَمَرُ لَا تَسْجُدُوا لِلشَّمْسِ وَلَا لِلْقَمَرِ وَاسْجُدُوا لِلَّهِ الَّذِي خَلَقَهُنَّ إِنْ كُنْتُمْ إِيَّاهُ تَعْبُدُونَ﴾

“ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው:: ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ:: ለእዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ:: እርሱን ብቻ የምትግገዙ እንደ ሆናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)::” (ፉሲለት ፡ 37)

ጥያቄ - 6፦ አሏህ የት ነው?

መልስ - 6፦ ከዐርሽ በላይ ሲሆን አላህ ከሰማይ በላይ ነው::

ጥያቄ - 7፦ እርሱ (በሚስማማው ሁኔታ) ከዐርሽ በላይ ሲሆን ከሰማይ በላይ ለመኖሩ ከቁርኣን ማስረጃው ምንድን ነው?

መልስ - 7፦ ከሰማይ በላይ ለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአሏህ ቃል ነው::

﴿ أَأَمِنْتُمْ مَنْ فِي السَّمَاءِ أَنْ يَخْسِفَ بِكُمُ الْأَرْضَ فَإِذَا هِيَ تَمُورُ ﴾

“ከሰማይ በላይ ያለን በእናንተ ምድርን ቢደረምስባችሁ ወዲያውኑ እርሷ የምታረገርግ ብትሆን ትተማመናላችሁ?” (ሙልክ ፡ 16)

ከአርሽ በላይ ለመሆኑ ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

﴿ الرَّحْمَٰنُ عَلَى الْعَرْشِ اسْتَوَى ﴾

“(እርሱ) አርረሕማን ፣ (እርሱ በሚስማማው ሁኔታ) ከአርሹ በላይ ሆነ።” (ጧሃ ፡ 5)

አላህ (ከእርሱ ጋር በሚስማማ ሁኔታ) ከአርሽ በላይ ለመሆኑ በቁርኣን ውስጥ በሰባት ቦታ ይገኛል

ጥያቄ - 8፦ “ኢስተዋ” የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

መልስ - 8፦ በላይ ሆነ፣ ከፍ አለ፣ ወጣ፣ ተደላደለ የሚሉ ትርጓሜዎች አሉት።

ጥያቄ - 9፦ ጅንን እና ሰውን አሏህ ለምን ፈጠራቸው?

መልስ - 9፦ ሳያጋሩ፣ እርሱን በብቸኛነት ለመገዛት ፈጠራቸው።

ጥያቄ - 10፦ ጅንን እና ሰውን አላህ እርሱን ለመገዛት መፍጠሩ ከቁርኣን ማስረጃው ምንድን ነው?

መልስ - 10፦ የሚከተለው የአሏህ ቃል ነው።

﴿ وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنْسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴾

“ጅንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም” (ዛሪያት ፡ 56)

ጥያቄ - 11፦ “የዕቡዱኒ” የሚለው ቃል ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ - 11፦ በአምልኮ እኔን ብቸኛ ሊያደርጉኝ ማለት ነው::

ጥያቄ - 12፦ “ዒባዳ” (አምልኮ) ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ - 12፦ ውጫዊም ይሁን ውስጣዊ ፣ ንግግሮችም ይሁኑ ተግባራት ፣ አሏህ ለሚወደውና ለሚቀበለው ሁሉ የተሰጠ አጠቃላይ ስም ነው::

ጥያቄ - 13፦ “ላኢላሃ ኢልለሏህ” የሚለው የምስክርነት ቃል ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ - 13፦ አሏህ እንጅ በእውነት የሚመለክ የለም ማለት ነው::

ጥያቄ - 14፦ “ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው” የሚለው የምስክርነት ቃል ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ - 14፦ ረሱል ባዘዙት ነገር መታዘዝ፣ የተናገሩትን ሁሉ እውነት ማለት፣ የከለከሉትንና ያስጠነቀቁትን ሁሉ መራቅ፣ እርሳቸው በደነገጉት ህግ እንጅ አላህን አለመገዛት ማለት ነው::

ጥያቄ - 15፦ አሏህ ካዘዘው ነገር ሁሉ ትልቁ ምንድን ነው?

መልስ - 15፦ አሏህ ካዘዘው ነገር ሁሉ ትልቁ ተውሒድ ነው። ተውሒድ ማለት ምንም ሳያጋሩ እርሱን በብቸኛነት መገዛት ማለት ነው።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፦

﴿ وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَسُولًا أَنِ اعْبُدُوا اللَّهَ وَاجْتَنِبُوا الطَّاغُوتَ

“በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ “አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ” በማለት መልእክተኛን በእርግጥ ልከናል።” (ነሕል ፡ 36)

ጥያቄ - 16፦ የተውሒድ ክፍሎች እነማን ናቸው?

መልስ - 16፦ “ተውሒድ አርሩቡቢያ” ፣ “ተውሒድ አልኡሉሂያ” እና “ተውሂድ አስማእ ወስሲፋት” ናቸው።

ጥያቄ - 17፦ “ተውሒድ አርሩቡቢያ” ትርጉሙ ምንድን ነው?

መልስ - 17፦ አላህን በተግባሩ ብቸኛ ማድረግ ነው። ለምሳሌ፦ በመፍጠሩ፣ በመመገቡ፣ ዝናብ በማውረዱ .... ወዘተ

ጥያቄ - 18፦ “ተውሒድ አልኡሉሂያ” (አምልኮትን ለአላህ ብቻ ማድረግ የሚለው እምነት) ትርጉሙ ምንድን ነው?

መልስ - 18፦ ባሮቹ፣ ለእነርሱ በደነገገላቸው መሰረት ተግባራቸውን በሙሉ ለአላህ ብቻ ማድረግ:: ለምሳሌ፦ ዱዓ (ጸሎት) ፣ እርድ፣ ስግደት...

ጥያቄ - 19፦ "ተውሒድ አልአስማእ ወስሲፋት" (ስሞችን እና ባህሪያትን ለአላህ ብቻ መነጠል የሚለው እምነት) ትርጉሙ ምንድን ነው?

መልስ - 19፦ በእርሱ በሚለይበት፣ ከስሞችም ይሁን ከባህሪያቱ አላህን ብቸኛ ማድረግ (ማለትም ለአላህ ብቻ ማድረግ) ማለት ነው::

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፦

لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ ۖ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ ﴾

"የሚመስለው ምንም ነገር የለም:: እርሱም ሰሚና ተመልካች ነው::" (ሹራ ፡ 11)

ጥያቄ - 20፦ ከአምልኮ አይነቶች ከፊሉን አውሳ?

መልስ - 20፦ ከአምልኮ አይነቶች መካከል፦ ዱዓ (ተማጽኖ)፣ ኢስቲጋሳ (የጭንቅ ጊዜ መማጸን)፣ ኢስቲዓና (እገዛን መፈለግ)፣ ዘብሁል ቁርባን (የመቃረቢያ እርድ)፣ ነዝር (ስለት)፣ ፍርሀት፣ ተስፋ፣ መመካት፣ ኢናባ (ተጸጽቶ መመለስ)፣ መሀባ (ውዴታ)፣ ኸሽያ (ፍርሀት)፣ ረግባ (እዝነቱን ከጅሎ አላህን መገዛት)፣ ረህባ (ቅጣቱን ፈርቶ አላህን መገዛት)፣ ሩኩዕ

(ማኅንበስ)፣ ሱጁድ (መደፋት)፣ ኹሹዕ (መተናነስ)፣ ተዘሉል (መዋረድ)፣ ዚክር፣ ቁርኣን መቅራት ይገኙበታል።

**ጥያቄ - 21፦ አላህ ከከለከላቸው ነገሮች ትልቁ ምንድን ነው?**

*መልስ - 21፦ ከከለከላቸው ነገሮች ትልቁ ሺርክ ወይም በአላህ ላይ ማጋራት ነው። ከአላህ ጋር ሌላን አካል ማምለክ ነው።*

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፦

﴿ إِنَّ اللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَنْ يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَنْ يَشَاءُ

"አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ በታች ያለውንም (ሐጢያት) ለሚሻው ሰው ይምራል።" (ኒሳዕ ፡ 48)

**ጥያቄ - 22፦ ሁለቱ የሺርክ (የማጋራት) ዓይነቶች እነማን ናቸው?**

*መልስ - 22፦ የመጀመሪያው የሺርክ ዓይነት፦ ትልቁ ሺርክ (ማጋራት) ነው። አላህ ወይም ረሱል ሺርክ (ማጋራት) ብለው የጠሩት እና ባለቤቱን ከኢስላም የሚያስወጣ ነው።*

ለምሳሌ፦ ጣዖታትን፣ ሙታንን ማምለክ፣ ከአላህ ውጭ ላለ አካል መስገድ ...

ሁለተኛው የሺርክ ዓይነት፦ ትንሹ ሺርክ ነው። ሺርክ በሚል ስያሜ የመጣና ባለቤቱን ከኢስላም የማያስወጣ ነው።

ለምሳሌ፦ ከአላህ ውጭ በሆነ አካል መማል፣ ቀላሉ የይዩልኝ፣ “ማሻአሏህ ወሺእተ” (አላህና አንተ የሻህው) የሚለው ንግግር ...

“ትንሹ ሺርክ” በሚል የተጠራበት ከትልቁ ሺርክ ላይ ለመውደቅ የሚያደርስ በመሆኑ ነው።

ጥያቄ - 23፦ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰዎች ዘንድ ሺርክ የተከሰተው መቼ ነው?

መልስ - 23፦ ለመጀመሪያ ጊዜ ሺርክ ከሰው ልጆች ዘንድ የተከሰተው በኑህ - ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም - ህዝቦች ነው (ማለትም ኑህ በተላከላቸው ህዝቦች ነው)።

ጥያቄ - 24፦ በኑህ - ዓለይሂሶላቱ ወሰላም - ህዝቦች ሺርክ የተከሰተበት ሰበብ (ምክንያት) ምንድን ነው?

መልስ - 24፦ የተከሰተበት ምክንያት፡ በደጋጎች ላይ ድንበር በማለፋቸው ነው።

ጥያቄ - 25፦ በደጋጎች ላይ ድንበር ማለፍ ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ - 25፦ ከአምልኮ አንዳችን ለእነርሱ አሳልፎ መስጠት፣ ከነበራቸው ደረጃ ከፍ ማድረግ፣ ከውዳሴያቸው ላይ ውዳሴን መጨመር ማለት ነው።

ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

يَا أَهْلَ الْكِتَابِ لَا تَغْلُوا فِي دِينِكُمْ

"እናንተ የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤" (ኒሳዕ ፡ 171)

የአላህ መልክተኛ - ዓለይሂሶላቱ ወሰላም - የሚከተለውን ተናግረዋል፦

"ክርስቲያኖች የመሬምን ልጅ ዒሳን ድንበር አልፈው እንዳወደሱት እኔንም ድንበር አሳልፋችሁ አታወድሱኝ። እኔ ባሪያ ነኝ። የአላህ ባሪያ መልክተኛው በሉኝ።" (ሐዲሱን ቡኻሪ ዘግበውታል)

"ላ ቱጥሩኒ" ማለት በውዳሴየ ላይ አትጨምሩ ማለት ነው።

ጥያቄ - 26፦ ሙታኖችን መጣራት ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 26፦ አላህ እንጅ ማንም በማይችለው ጉዳይ ሙታኖችንም ይሁን ሌሎችን አካላት መጥራት ከኢስላም የሚያስወጣ ትልቁ ሺርክ ነው።

ማስረጃው ቁርኣን ነው፦

﴿ وَمَنْ يَدْعُ مَعَ اللَّهِ إِلَٰهًا آخَرَ لَا بُرْهَانَ لَهُ بِهِ فَإِنَّمَا حِسَابُهُ عِنْدَ رَبِّهِ ۚ إِنَّهُ لَا يُفْلِحُ الْكَافِرُونَ ﴾

"ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ ለእርሱ በእርሱ ማስረጃ የሌለውን የሚገዛ ሰው ምርመራው ከጌታው ዘንድ ብቻ ነው:: እነሆ ከሀዲዎች አይድኑም፤" (አልሙእሚኑን 117)

ጥያቄ - 27፦ አላህን ለመማጸን የፍጡራን አማላጅነት ይፈልጋል?

መልስ - 27፦ አላህን ለመማጸን የፍጡሮች ምልጃ አያስፈልገውም::

ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፦

﴿ وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِي عَنِّي فَإِنِّي قَرِيبٌ ۖ أُجِيبُ دَعْوَةَ الدَّاعِ إِذَا دَعَانِ ۖ فَلْيَسْتَجِيبُوا لِي وَلْيُؤْمِنُوا بِي لَعَلَّهُمْ يَرْشُدُونَ ﴾

"ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው) ፦ እኔ ቅርብ ነኝ ፤ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ:: " (አልበቀራ ፡ 186)

ጥያቄ - 28፦ ሙታኖች ለጥሪ ምላሽ መስጠት ይችላሉን?

መልስ - 28፦ ሙታኖች ለጥሪ ምላሽ አይሰጡም::

ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

﴿إِنْ تَدْعُوهُمْ لَا يَسْمَعُوا دُعَاءَكُمْ وَلَوْ سَمِعُوا مَا اسْتَجَابُوا لَكُمْ وَيَوْمَ الْقِيَامَةِ يَكْفُرُونَ بِشِرْكِكُمْ

**"ብትጠሯቸው ጥሪያችሁን አይሰሙም:: ቢሰሙም ኖሮ ለእናንተ አይመልሱላችሁም:: በትንሳኤ ቀን (እነርሱን በአላህ) ማጋራታችሁን ይክዳሉ ::" (ፋጢር ፡ 14)**

**ጥያቄ - 29፡- የምናርደውና የምንሰግደው ለማን ነው?**

***መልስ - 29፡- የምናርደው ብቸኛና ተጋሪ ለሌው አምላክ ለአላህ ብቻ ነው::***

**አላህ በቁርኣን የሚተከለውን ተናግሯል፡-**

﴿ فَصَلِّ لِرَبِّكَ وَانْحَرْ ﴾

**"ስለዚህ ለጌታህ ስገድ ፤ (በስሙ) ሰዋም::" (ከውሠር ፡ 2)**

**ጥያቄ - 30፡- ከአሏህ ውጭ ማረድ እና መስገድ ብይኑ ምንድን ነው?**

***መልስ - 30፡- ከአላህ ውጭ ማረድና መስገድ ከእስልምና ሐይማኖት የሚያስወጣ ትልቁ ማጋራት ነው::***

***ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፡-***

﴿ قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ ۝ لَا شَرِيكَ لَهُ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ ﴾

“ስግደቴ፣ እርዴ፣ ሕይዎቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው” በል:: “ለእርሱ ተጋሪ የለውም:: በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ፣ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ::” በል:: (አንዓም ፡ 162-163)

“ኑሱኪ” ማለት እርዴ ማለት ነው::

ጥያቄ - 31፦ ከአላህ ውጭ መማል ብይኑ ምንድን ነው? ለምሳሌ፦ በነብዩ ወይም በአደራ ወይም በልቅና ወይም በሌላ መማል?

መልስ - 31፦ ከአላህ ውጭ መማል ብይኑ፦ ትንሹ ማጋራት ነው::

የአላህ መልክተኛ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፦

“መማል የፈለገ ሰው በአላህ ብቻ ይማል ወይም ዝም ይበል” (ሐዲሱን ቡኻሪ ዘግበውታል)

ጥያቄ - 32፦ የአላህን ስሞችና ባህሪያት አስመልክቶ በሙስሊም ላይ ያለው ግዴታ ምንድን ነው?

መልስ - 32፦ ከስሞቹና ከባህሪያቶቹ ያለምንም ማጣመም፣ ያለማራቆት፣ አኳኋኑ እንዲህ ነው ያለማለት እና ያለማመሳሰል አሏህ ለነፍሱ ያጸደቀውን ማጽደቅ፤ ረሱል ለእርሱ ያጸደቁትን ማጽደቅ ነው:: አሏህ ከነፍሱ ላይ ያራቆተውን ማራቆት፣ ረሱል ከእርሱ ላይ ያራቆቱትን ማራቆት ነው::

ጥያቄ - 33፦ የአላህ ባህሪያት ከእኛ ባህሪያት ጋር የማይመሳሰሉ ለመሆናቸው ከቁርኣን ማስረጃው ምንድን ነው?

መልስ - 33፦ ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ

"የሚመስለው ምንም ነገር የለም:: እርሱም ሰሚና ተመልካች ነው::" (ሹራ ፡ 11)

ጥያቄ - 34፦ እምነትህ ምንድን ነው?

መልስ - 34፦ እምነቴ እስልምና ነው::

ለዚህ ማስረጃ የአላህ ቃል ነው፦

﴿ إِنَّ الدِّينَ عِنْدَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ

"አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው::" (አልኢምራን ፡ 19)

ጥያቄ - 35፦ ነቢዩ ሙሐመድ ከተላኩ በኋላ ከእስልምና ውጭ ሀይማኖትን አላህ ይቀበላልን?

መልስ - 35፦ ረሱል - ዓለይሂሶላቱ ወሰላም - ከተላኩ በኋላ ከእስልምና ሀይማኖት ውጭ ሀይማኖትን አላህ አይቀበልም::

ማስረጃችን የአላህ ቃል ነው፦

﴿ وَمَنْ يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَنْ يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي الْآخِرَةِ مِنَ الْخَاسِرِينَ

“ከኢስላም ሌላ ሀይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፤” (አልኢምራን ፡ 85)

ጥያቄ - 36፦ የኢስላም ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ - 36፦ እርሱ (ትርጉሙ) በተውሒድ ለአላህ ታዛዥ መሆን፣ በመታዘዝ ለእርሱ ተገታች መሆን፣ ከማጋራት እና ከማጋራት ባለቤቶች መጽዳት ማለት ነው።

ጥያቄ - 37፦ የኢስላም ማእዘናቶች እነማን ናቸው?

መልስ - 37፦ ከአላህ በቀር - በእውነት የሚመለክ - አምላክ አለመኖሩን፣ ሙሐመድ የአላህ ባሪያ እና መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሶላትን (ደንቡን ጠብቆ) መስገድ፣ ዘካ መስጠት፣ ረመዷንን መጾም፣ ወደርሱ መንገድን ለቻለ ቤቱን መጎብኘት።

ማስረጃው የረሱል ንግግር ነው፦

“ኢስላም ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የሌለ መሆኑ ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሶላት (ደንቡን ጠብቆ) መስገድ፣ ዘካ መስጠት፣ ረመዷንን መጾም፣ መንገድን ከቻልህ ቤቱን መጎብኘት።” (ሐዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ጥያቄ - 38፦ የኢማን ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ - 38፦ ኢማን በአንደበት በመናገር፣ በልብ በማመን፣ በአካል በመተግበር ይገለጻል። ኢማን አላህን በመታዘዝ ይጨምራል፣ ወንጀል በመፈጸም ይቀንሳል።

ጥያቄ - 39፦ የኢማን ማእዘናቶች እነማን ናቸው?

መልስ - 39፦ በአላህ፣ በመላኢካዎች፣ በመጽሐፎቹ፣ በመልክተኞች፣ በመጨረሻው ቀን፣ መልካምም ይሁን ክፉ በአላህ ውሳኔ ማመን ናቸው።

ማስረጃው የረሱል ቃል ነው፦

“እምነት በአላህ፣ በመላኢካዎች፣ በመጽሐፉ፣ በመልክተኞች፣ በመጨረሻው ቀን፣ መልካምም ይሁን ክፉ በአላህ ውሳኔ ልታምን ነው።” (ሐዲሱን ሙስሊም ዘግቦታል)

ጥያቄ - 40፦ መላኢካዎች ምንድን ናቸው?

መልስ - 40፦ መላኢካዎች አላህ ለአምልኮ የፈጠራቸው ስውር ፍጥረቶች ናቸው።

ጥያቄ - 41፦ በመላኢካዎች ማመን ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 41፦ በመላኢካዎች ማመን ግዴታ ነው። በእነርሱ በማመን እንጅ እምነት ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም።

ጥያቄ - 42፦ ከመላኢካዎች መካከል በላጩ ማን ነው?

መልስ - 42፦ ጂብሪል - ዓለይሂሰላም - ነው። እርሱም ወህይ በማውረድ ውክልና የተሰጠው ነው።

ጥያቄ - 43፦ ከሰማይ የወረዱ መጽሐፎች ማን ናቸው?

መልስ - 43፦ በመልክተኞች ላይ - አለይሂሙሰላም - አላህ ያወረዳቸው መጽሀፎች ናቸው። ለምሳሌ፦ ተውራት፣ ኢንጂል፣ ዘቡር እና ቁርኣን ናቸው።

ጥያቄ - 44፦ በመጽሐፎች ማመን ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 44፦ በመጽሐፎች ማመን ግዴታ ነው። በእርሱ በማመን እንጅ እምነት ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም።

ጥያቄ - 45፦ ከሰማይ ከወረዱ መጽሐፎች ትልቁ ማን ነው?

መልስ - 45፦ ከወረዱ መጽሐፎች ሁሉ ትልቁ፦ በነቢዩ ሙሐመድ - ዓለይሂሶላቱ ወሰላም - ላይ አላህ ያወረደው ቁርኣን ነው።

ሁሉንም ከሰማይ የወረዱ መጽሐፎችን የሻረ ነው:: በእርሱ እንጅ አላህን መገዛት አይቻልም::

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፦

﴿ وَأَنْزَلْنَا إِلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ الْكِتَابِ وَمُهَيْمِنًا عَلَيْهِ ﴾

"ወደ አንተም መጽሐፍን (ቁርኣንን) ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በእውነት አወረድን::" (ማኢዳ ፡ 48)

ጥያቄ - 46፦ የመጨረሻው ቀን ምንድን ነው?

መልስ - 46፦ እርሱ ዋጋ እና ምንዳ ለመሰጠት ሰዎች የሚቀሰቀሱበት የቂያማ ቀን ነው::

ጥያቄ - 47፦ በመጨረሻው ቀን ማመን ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 47፦ በመጨረሻው ቀን ማመን ግዴታ ነው:: በእርሱ በማመን እንጅ ኢማን ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም::

ጥያቄ - 48፦ በቀደር ማመን ምንድን ነው?

መልስ - 48፦ ቀደር፦ ጥበቡ ባስፈረደውና ቀዳማዊ በሆነው እውቀቱ መሰረት ለፍጡራኖች የአላህ መወሰን ነው::

ጥያቄ - 49፦ በቀደር ማመን ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 49፦ በቀደር ማመን ግዴታ ነው። በእርሱ በማመን እንጅ እምነት ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።

ጥያቄ - 50፦ ኢህሳን (አምልኮትን ማሳመር) ምንድን ነው?

መልስ - 50፦ ኢህሳን፦ ልክ እንደምታየው ሆነህ አላህን መገዛት ነው። አንተ ባታየው እንኳ እርሱ ይመለከትሀልና።

ጥያቄ - 51፦ የ "ሪያእ" (ይዩልኝ) ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ - 51፦ "ሪያእ" ማለት ሰዎች እንዲያወድሱትና እንዲመለከቱት ብሎ አምልኮትን መፈጸም ማለት ነው።

ጥያቄ - 52፦ የ "ሪያእ" (ይዩልኝ) ብይን ምንድን ነው?

መልስ - 52፦ "ሪያእ" (ይዩልኝ) እርም ነው። እርሱም ከትንሹ ማጋራት ነው።

ማስረጃው የነብዩ ንግግር ነው፦

"በእናንተ ላይ ከምፈራው ሁሉ በጣም የምፈራው ትንሹን ማጋራት ነው።" በማለት ነብዩ ተናገሩ። ስለርሱም ጥያቄ ቀረበላቸው። "ሪያእ" (ይዩልኝ) ነው

በማለት ምላሽ ሰጡ::" (ሐዲሱን አህመድ ዘግቦታል:: አልባኒም ሶሒህ (ትክክለኛ ሐዲስ) ብለውታል)

ጥያቄ - 53፦ ነብይህ ማን ነው?

መልስ - 53፦ ነብዬ፡ እርሱ ሙሐመድ ብን ዐብዲላህ ብን ዐብዱልሙጦሊብ ብን ሃሺም ነው:: ሃሺም ከቁረይሽ ነው:: ቁረይሽ ደግሞ ከኪናና ነው:: ኪናና ደግሞ ከዐረቦች ነው:: ዐረቦች የኢስማኢል ዝርዮች ናቸው:: ኢስማኢል የኢብራሂም ዐለይሂሶላቱ ወሰላም ልጅ ነው::

ጥያቄ - 54፦ ነብዩ ሙሐመድ ነብይ ለመሆናቸው ትልቁ ምልክት ምንድን ነው?

መልስ - 54፦ ለነብይነታቸው ትልቁ ምልክት ታላቁ ቁርኣን ነው:: እርሱ ብርሀን፣ መድሀኒት፣ መሪ የሆነ የአላህ ንግግር ነው::

ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

﴿ قُلْ لَئِنِ اجْتَمَعَتِ الْإِنْسُ وَالْجِنُّ عَلَىٰ أَنْ يَأْتُوا بِمِثْلِ هَٰذَا الْقُرْآنِ لَا يَأْتُونَ بِمِثْلِهِ وَلَوْ كَانَ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ ظَهِيرًا ﴾

"ሰዎችም ጅኖችም የዚህን ቁርኣን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰባሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢሆንም እንኳ ብጤውን አያመጡም" በላቸው:: (አልኢስራእ ፡ 88)

ጥያቄ - 55፦ ከነብዩ ሙሐመድ መብቶች መካከል ትልቁ ማን ነው?

መልስ - 55፦ ከነብዩ ሙሐመድ መብቶች መካከል ትልቁ፦ በእርሳቸው እውነተኛ የሆነ እምነት ማመን፤ በአጠቃላይ ለሰው ልጆችም ይሁን ለጅን አላህ የላካቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣ እርሳቸውን መታዘዝ ግዴታ ሲሆን እርሳቸውን ከመንቀፍ መጠንቀቅ፣ እርሳቸውን መከተል፣ በእርሳቸው መመራት፣ ሱናቸውን ማላቅ፣ ከቤተሰብ፣ ከልጅ፣ ከአጠቃላይ ከሰዎች አብልጦ እርሳቸውን መውደድ። እርሳቸውን ማክበር፣ በእርሳቸው ላይ ሶለዋት ማውረድ፤ በእርሳቸው ድንበር አለማለፍ፣ አላህ ካስቀመጣቸው ደረጃ ከፍ አለማድረግ ናቸው።

ጥያቄ - 56፦ ድግምት ምንድን ነው?

መልስ - 56፦ ድግምት ማለት በአካልም ይሁን በልቦና ላይ በትክክል (በአላህ ፈቃድ) ተጽእኖ የሚያሳድር የሰይጣን ስራ ነው። ከዚህ መካከል ትክክለኛነት የሌለው በአይን ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ብዥታ የሚፈጥርም አለ።

ጥያቄ - 57፦ ጥንቆላ ማለት ምንድን ነው?

መልስ - 57፦ ጥንቆላ ማለት በጅን በመታገዝ ስውር እውቀቶችን አውቃለሁ ብሎ መሞገት ነው።

ጥያቄ - 58፦ “ዓርራፍ”(የሩቅ አዋቂ ነን ባዩች) ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ - 58፦ “ዓርራፍ” ማለት በተሰረቀው እቃና ያለበትን ቦታ ቅድመ መረጃዎች ላይ ተንተርሶ የሩቅ ነገሮችን አውቃለሁ ብሎ የሚሞግት ነው።

“አርራፍ” ማለት፦ ለጠንቋይ፣ ለኮከብ ቆጣሪ፣ ለጠጠር ወርዋሪ እና ለመሳሰሉ በጅን አማካኝነት የሩቅ ነገሮችን እናውቃለን ብለው ለሚናገሩ ሰዎች የተሰጠ ስያሜ ነውም ተብሏል።

ከተግባራቶቻቸው መካከል፦ ኮከብ በመቁጠር፣ በመዳፍ እና በሲኒ ላይ በማንበብ እና በመሳሰሉ ነገሮች በመታገዝ የሩቅ ነገሮችን እናውቃለን ብለው ይሞግታሉ።

ጥያቄ - 59፦ ወደአርራፍ፣ ካሂን እና ሌሎችም የሩቅ ሚስጢር እናውቃለን ብለው ወደሚሞግቱ አካላት መሄድ ፍርዱ ምንድን ነው?

መልስ - 59፦ ወደድግምተኛ፣ ወደአርራፍ፣ ወደካሂን (ጠንቋይ) መሄድ እርም ነው።

ትክክለኛ በሆነው የሙስሊም ዘገባ ረሱል (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“ወደአርራፍ (የሩቅ ሚስጢር አዋቂ ነን ወደሚሉ ሰዎች) ሄዶ ከዚያም ስለአንድ ነገር ጠንቋዩን የጠየቀ የአርባ ሌሊት ሶላቱ ተቀባይነት አያገኝም::”

አቡሁረይራ ከረሱል (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሰምቶ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፏል፦

“ወደአርራፍ ወይም ጠንቋይ ሄዶ ጠንቋዩ የሚለውን ነገር እውነት ያለ፣ በሙሐመድ በተወረደው በእርግጥ ካደ::” (አህመድ፣ አቡዳውድ እና ቲርሚዝይ ዘግበውታል)

ጥያቄ - 60፦ ድግምትና እርሱን መማር ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 60፦ ድግምት በአጠቃላይ እርምና ክህደት ነው:: መማሩም ማስተማሩም:: ከእርሱም አንዱም አይፈቀድም::

ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

وَمَا كَفَرَ سُلَيْمَانُ وَلَٰكِنَّ الشَّيَاطِينَ كَفَرُوا يُعَلِّمُونَ النَّاسَ السِّحْرَ

“ሱለይማንም አልካደም (ድግምተኛ አልነበረም)፤ ግን ሰይጣናት ሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ ሲሆኑ ካዱ::” (በቀራ ፡ 102)

ጥያቄ - 61፦ በከዋክብቶች እድልን መፈለግ፣ እርሱንም መማር፣ የወደፊቱን መተንበይ፣ እርሱንም እውነት ብሎ ማመን ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 61፦ እርሱ የጃሂልያ ማህበረሰብ ተግባር ነው። የሩቁን እውቀት እናውቃለን ብለው በመሞገት ከኮከብ ቆጣሪዎች እና አርራፎች (ጠንቋዩች) ውስጥ ይካተታል።

ረሱል (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“ከከዋክብት እውቀት ዘርፍ አንዱን የቀሰመ፣ በእርግጥም ከድግምት እውቀት ቀሰመ። ከጨመረም (ክህደቱም) ይጨምራል” (ትክክለኛ በሆነ ሰነድ አቡዳውድ ዘግቦታል)

ጥያቄ - 62፦ “ተማኢም” (አሽንኪታብ) ምንድን ነው?

መልስ - 62፦ “ተማኢም”፣ የ “ተሚማ” ጀምእ (ብዙን ቁጥር የሚያመላክት) ሲሆን እርሱም ሂርዞች (እንደሙስበሃ የተሰካኩ) ወይም አጥንቶች፣ ወይም ጽሑፎች ወይም ሲሮች ወይም ገመዶች ወይም የተቀዳደዱ ጨርቆች ወይም ሌሎችም ናቸው። ከህጻናት አንገቶች ላይ ይንጠለጠላሉ ወይም ከጡንቻ ወይም ከቤቶች ወይም ከመኪናዎች ላይ ይንጠለጠላሉ። አላማው ከመከሰቱ በፊት መከራን ለመከላከል፣ ከተከሰተ በኋላም ቢሆን መከራው እንዲነሳ በሚል ነው።

ጥያቄ - 63፦ የ "ተማኢም" ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 63፦ "ተማኢም" (ሂርዝ ማንጠልጠል) ትንሹ ማጋራት ነው። አንዳንዴ ከአላህ ውጭ ይጠቅማል ይጎዳል የሚል እምነት ካለው ትልቁ ማጋራት ሊሆን ይችላል።

ለዚህ ማስረጃው የረሱል - ዓለይሂሶለቱ ወሰላም - ንግግር ነው፦

"ተሚማን ያንጠለጠለ በእርግጥ አጋራ" አህመድ ዘግበውታል አልባኒ ትክክል ነው ብለዋል።

ጥያቄ - 64፦ ሸሪዓዊ ሩቃ ምንድን ነው? ብይኑስ?

መልስ - 64፦ ቁርኣን ወይም ዱዓ በበሽተኛው ላይ ማንበብ ማለት ነው። ከታመመበት ቦታ (ቁርኣን እያነበቡ) ትፍ፤ትፍ ማለት ነው። (ሸሪዓዊ) ሩቃ የተፈቀደ ነው።

የአላህ መልክተኛ - ዓለይሂሶለቱ ወሰላም - የሚከተለውን ተናግረዋል፦

"ማጋራት ከሌለበት ሩቃ ችግር የለውም።" (ሙስሊም ዘግቦታል)

እርሱን ለመፍቀድ፡ ከሺርክ መጽዳቱ፣ ሰበብ እንጅ በራሷ ተጽእኖ የማሳደር አቅም የሌለው መሆኑን ማመኑ፣ መጥቀምም መጉዳትም በአላህ እጅ መሆኑን

ማመኑ፣ በዐረብኛ ቋንቋ ወይም ከሌላው ከሆነ ትርጉሙ በሚታወቅ መሆኑ፣ በአላህ ቃል ወይም በስሞቹ እና በባህሪያቶቹ መሆኑ መስፈርት ይደረጋል።

ጥያቄ - 65፦ "ጢየራ" (የገድ አምልኮ) ምንድን ነው?

መልስ - 65፦ "ጢየራ" ማለት ተስፈኝነት ወይም በወፎች ገደ ቢስ አምልኮ ማለት ነው።

ጥያቄ - 66፦ ከማስረጃ ጋር ብይኗ ምንድን ነው?

መልስ - 66፦ የገድ አምልኮ እርም ነች፣ ከትንሹ ማጋራትም ነች። ''ከአላህ ውጭ ትጠቅማለች፣ ትጎዳለች'' የሚል እምነት ካለው ከትልቁ ማጋራትም ልትሆን ትችላለች።

ማስረጃው የረሱል (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ንግግር ነው፦

"ጢየራ (የገድ አምልኮ) ሺርክ ነው" (አህመድ እና አቡዳውድ ዘግበውታል)

ጥያቄ - 67፦ ከወፎች ውጭ "ጢየራ" (የገድ አምልኮ) ሊከሰት ይችላልን?

መልስ - 67፦ አዎ፣ በአንዳንድ ወፎች ወይም ቀናቶች ወይም እንስሳት ወይም የባህሪያት ባለቤት በሆኑ አካላቶች - እውርነት ፣ ሽባነት እና በሌሎችም ገደ ቢስ መሆን እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።

ጥያቄ - 68፦ በከዋክብት ኢስቲስቃእ (በከዋክብት ዝናብን መፈለግ) ትርጉሙ ምንድን ነው?

መልስ - 68፦ “አንዋእ” ማለት ከዋክብት ናቸው።

ከከዋክብት ዝናብን መፈለግ ማለት ዝናብ ከላይ በወረደ ጊዜ፤ የዝናቡን መዝነብ ወደርሷ (ወደከዋክብት) ማዛመድ ማለት ነው።

ጥያቄ - 69፦ በከዋክብት ዝናብን መፈለግ ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 69፦ በሁለት ይከፈላል።

**የመጀመሪያው፦** ከዋክብት ዝናብን ያወርዳሉ ብሎ ማመን ነው። ይህ ከሆነ ክህደት ነው - ምክንያቱም በአላህ (ብቸኛ አስተናባሪነት) ማጋራት በመሆኑ።

**ሁለተኛው፦** ዝናብን የሚፈጥር ወይም የሚያወርደው አላህ ነው ነገር ግን ከዋክብት ምክንያቶች ናቸው ብሎ ማመን ነው። ይህ የአላህን ጸጋ ከአላህ ውጭ በማዛመዱ ትንሹ ማጋራት ነው - ምክንያቱም አላህ (ዝናብ ለመዝነቡ) ከዋክብትን ምክንያት አላደረገምና።

ጥያቄ - 70፦ በከዋክብት ዝናብን መፈለግ እርም ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው?

መልስ - 70፦ ማስረጃው የነብዩ ንግግር ነው።

“በአላህ ችሮታና በእዝነቱ ተዘነበልን በማለት የተናገረ፣ ይህ በእኔ ያመነ፣ በከዋክብት የካደ ነው። በዚህ በዚህ ኮከብ ተዘነበልን በማለት የተናገረ ይህ በእኔ የካደ በከዋክብት ያመነ ነው።” በማለት አላህ ተናገረ ሲሉ ረሱል (በሐዲሰል ቁድስ) ተናገሩ። (ሐዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ጥያቄ - 71፦ ከመቃብሮች ላይ መስጊዶችን መገንባት ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 71፦ ከመቃብሮች ላይ መስጊዶችን መገንባት እርም ነው። ወደ ሺርክ (ማጋራት) ያደርሳል።

የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“በአይሁዶችና ነሷራዎች ላይ የአላህ እርግማን ይውረድባቸው የነብያቶችን መቃብሮች መስጊድ አድርገው ያዙ” (ሐዲሱን ቡኻሪ ዘግበውታል)

ጥያቄ - 72፦ የ “ተበሩክ” ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ - 72፦ “ተበሩክ” ማለት በረካን መፈለግ ማለት ነው። በረካ መልካም ነገር መገኘቱና መዘውተሩ ነው።

ጥያቄ - 73፦ የ “ተበሩክ” ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

መልስ - 73፦ **አንደኛው፦** ሸሪኣዊ የሆነው ተበሩክ ነው:: እርሱም የሚፈቀደው አይነት ነው:: ይህ አይነቱ የቁርኣን እና የሱና ማስረጃዎች የሚጠቁሙት ነው::

**ሁለተኛው** አይነት፦ ክልክል የሆነው ተበሩክ ነው:: እርሱም እርም የሆነው አይነት ነው

ጥያቄ - 74፦ ሸሪዓዊ የሆነው የተበሩክ አይነት ምንድን ነው?

መልስ - 74፦ ሸሪዓዊ የሆነው ተበሩክ ሁለት አይነት ነው

**አንደኛው፦** ቁሳዊና በሚዳሰሱ ነገሮች ተበሩክ ማድረግ ነው:: ለምሳሌ፦ በዘምዘም ውሃ ተበሩክ ማድረግ::

**ሁለተኛው፦** በመልካም ስራዎች ተበሩክ ማድረግ ነው:: ለምሳሌ፦ በሶላት፣ በዱዓ እና በሶደቃ ተበሩክ ማድረግ::

ጥያቄ - 75፦ ክልክል የሆነው የተበሩክ አይነት ምንድን ነው?

መልስ - 75፦ ክልክል የሆነው ተበሩክ ሁለት አይነት ነው

**አንደኛው፦** ሸሪዓው የከለከለው ነው:: ለምሳሌ፦ በጣኦትና በሀውልት ተበሩክ ማድረግ::

**ሁለተኛው፦** እውነታ የሌለው ምናባዊ ምክንያቶች መካከል የሆነው ነው።

ለምሳሌ፦ በደጋጎች አካል ተበሩክ ማድረግ፣ ወይም በልብሳቸው፣ በልጋጋቸው (ከአፋቸው በሚወጣው ፈሳሽ) ፣ በዛፎችና በዲንጋዮች ተበሩክ ማድረግ።

ጥያቄ - 76፦ በዱዓ መቃረብ ክፍሎቹ ምን ምን ናቸው?

መልስ - 76፦ በዱዓ መቃረብ በሁለት ይከፈላል።

**አንደኛው፦** ህጋዊ የሆነ መቃረብ ነው። እርሱም ሸሪዓዊ መረጃዎች የጠቆሙት ነው።

**ሁለተኛው፦** ክልክል የሆነው መቃረብ ነው። እርሱም ሸሪዓዊ መረጃዎች ያልጠቆሙት ወይም የከለከሉት ነው።

ጥያቄ - 77፦ በዱዓ ህጋዊ የመቃረብ አይነቶች እነማን ናቸው?

መልስ - 77፦ በዱዓ ሸሪዓዊ የመቃረብ አይነቶች ሶስት አይነቶች ናቸው።

**አንደኛው** - በአላህ ስሞችና ባህሪያቶች መቃረብ። ለምሳሌ "ያ ረህማን፣ እርሀምኒ" (አዛኝ የሆንከው ጌታ እዘንልኝ) ማለትን ይመስል።

**ሁለተኛው** - በመልካም ስራ መቃረብ ነው።

ለምሳሌ የሚከተለው የአላህ ቃል ፦

الَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا إِنَّنَا آمَنَّا فَاغْفِرْ لَنَا ذُنُوبَنَا وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ

“ጌታችን ሆይ! እኛ አመንን ሐጢያቶቻችንንም ለእኛ ማር፣ የእሳት ቅጣትን ጠብቀን” የሚሉ ናቸው” (አልኢምራን ፡ 16)

**ሶስተኛው፦** በህይወት ያለ፣ በአካል የተገኘን አካል ዱዓን ከእርሱ በመፈለግ መቃረብ። ለዚህ ምሳሌ ኡካሻ የሰራው ነው። ያለምንም ሂሳብ ጀነት ከሚገቡ ሰባ ሺህ ሰዎች መካከል ለመሆን “ከእነርሱ እንዲያደርገኝ አላህን ለምኑልኝ” በማለት ነብዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ጠየቃቸው። የአላህ መልክተኛም (አንተ ከእነርሱ ነህ) አሉት። ሐዲሱን (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።)

ጥያቄ - 78፦ በዱዓ ክልክል የሆነው መቃረብ አይነቶች እነማን ናቸው?

መልስ - 78፦ አንደኛው፦ ሺርክ የሆነው መቃረብ ነው። በአላህ ማጋራት በውስጡ የተካተተበት መቃረብ ነው። በደጋግ ሰዎች እርዳታን መጠየቅ፣ ከአላህ ውጭ እነርሱን መለመን። ለምሳሌ፦ “የአላህ መልክተኛ ሆይ! እርዱኝ” ወይም “ጀይላኒ ሆይ! እገዙኝ” ማለት።

**ሁለተኛው፦** አዲስ ፈጠራ የሆነ መቃረብ ነው:: ሸሪዓዊ መረጃዎች በማይጠቁሙት መንገድ የሚደረግ መቃረብ ነው:: ምክንያቱም መቃረብ አምልኮ ነው:: በሸሪዓ መረጃ ካልሆነ በቀር አንዳችም ነገር አይፈቀድም:: በደጋግ ሰዎች አካል ወይም ልቅና የሚደረገው መቃረብ ቢድዓ ከሆነው መቃረቢያ ዓይነት ነው::

ጥያቄ - 79፦ በትንሳኤ ቀን ተፈጻሚ የሚሆነው ምልጃ ምንድን ነው?

መልስ - 79፦ እርሱም ለአንድ አካል ጥቅም ለማምጣት፣ ወይም ጉዳትን ከእርሱ ላይ ለመከላከል ከአላህ ዘንድ ተፈጻሚ የሚሆን ምልጃ ነው

ጥያቄ - 80፦ ከሙታን ምልጃ ይፈለጋልን?

መልስ - 80፦ ከሙታን ምልጃ አይፈለግም:: ምክንያቱም ምልጃ የአላህ ብቻ ነች::

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፦

قُلْ لِلَّهِ الشَّفَاعَةُ جَمِيعًا

“ምልጃ በአጠቃላይ የአላህ ብቻ ነው” (ዙመር ፡ 44)

ጥያቄ - 81፦ የምልጃ መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

መልስ - 81፦ የምልጃ መስፈርቶች ሁለት ናቸው፦

አንደኛው፦ አማላጁ ለማማለድ የአላህን ፈቃድ ማግኘት።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፦

مَنْ ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِنْدَهُ إِلَّا بِإِذْنِهِ

“ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማን ነው?” (በቀራ ፡ 255)

**ሁለተኛው፦** የሚማለዱለት አካል ከአላህ ዘንድ ተወዳጅ መሆኑ ነው።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፦

وَلَا يَشْفَعُونَ إِلَّا لِمَنِ ارْتَضَىٰ ...

“ለወደደውም ሰው እንጅ ለሌላው አያማልዱም” (አንቢያእ ፡ 28)

ጥያቄ - 82፦ ምልጃ የሚያገኘው ማን ነው?

መልስ - 82፦ ምልጃ ለተውሂድ ሰዎች ብቻ ነው የሚሆነው።

ማስረጃው የነብዩ ንግግር ነው፦

“የቂያማ ቀን በእኔ ምልጃ ከሰዎች በጣም እድለኛው ከልቡ አጥርቶ ላኢላሃ ኢልለላህ ያለ ሰው ነው” (ሐዲሱን ቡኻሪ ዘግበውታል)

**ጥያቄ - 83፦ በአላህ፣ በቁርኣኑ፣ በዲኑ እና በመልክተኛው የተሳለቀ ሰው ብይኑ ምንድን ነው?**

**መልስ - 83፦ ከእነዚህ ነገሮች በአንዱ የተሳለቀ ብይኑ ከሐዲ መሆን ነው::**

**ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፦**

قُلْ أَبِاللَّهِ وَآيَاتِهِ وَرَسُولِهِ كُنْتُمْ تَسْتَهْزِئُونَ ۞ لَا تَعْتَذِرُوا قَدْ كَفَرْتُمْ بَعْدَ إِيمَانِكُمْ

**“በአላህና በአንቀጾቹ በመልክተኛውም ታላግጡ ነበራችሁን በላቸው:: አታመካኙ ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ካዳችሁ::” (ተውባ፡ 65 - 66)**

**ጥያቄ - 84፦ “ወላእ” እና “በራእ” ትርጉማቸው ምንድን ነው?**

**መልስ - 84፦ “ወላእ” ማለት ለአላህ፣ ለመልክተኛው ለሙስሊሞች መውደድ መርዳት ማለት ነው::**

**ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦**

﴿ إِنَّمَا وَلِيُّكُمُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ وَالَّذِينَ آمَنُوا الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَيُؤْتُونَ الزَّكَاةَ وَهُمْ رَاكِعُونَ ۞ وَمَنْ يَتَوَلَّ اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَالَّذِينَ آمَنُوا فَإِنَّ حِزْبَ اللَّهِ هُمُ الْغَالِبُونَ

**“ረዳታችሁ አላህና መልክተኛው እነዚያም ያመኑት ብቻ ናቸው:: (እነርሱ) እነዚያ ሶላትን በደንቡ የሚሰግዱ**

እነርሱም ራሳቸውን ያስተናነሱ ሆነው ምጽዋትን የሚሰጡ ናቸው:: አላህንና መልክተኛውን እነዚያንም ያመኑትን የሚወዳጅ ሰው (ከአላህ ጭፍሮች ይሆናል):: የአላህም ጭፍሮች አሸናፊዎች እነርሱ ብቻ ናቸው::" (ማኢዳ፡ 55-56)

"በራእ" ማለት ክህደትን እና ከሀዲዎችን መጥላትና ጠላት ማድረግ ማለት ነው::

ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፦

﴿ قَدْ كَانَتْ لَكُمْ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ فِي إِبْرَاهِيمَ وَالَّذِينَ مَعَهُ إِذْ قَالُوا لِقَوْمِهِمْ إِنَّا بُرَآءُ مِنْكُمْ وَمِمَّا تَعْبُدُونَ مِنْ دُونِ اللَّهِ كَفَرْنَا بِكُمْ وَبَدَا بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمُ الْعَدَاوَةُ وَالْبَغْضَاءُ أَبَدًا حَتَّىٰ تُؤْمِنُوا بِاللَّهِ وَحْدَهُ

"በኢብራሂምና በእነዚያ ከእርሱ ጋር በነበሩት (ምእምናን) መልካም መከተል አለቻችሁ:: ለሕዝቦቻቸው «እኛ ከእናንተ ከአላህ ሌላ ከምትግገዙትም ንጹሖች ነን፡ በእናንተ ካድን:: በአላህ አንድ ብቻ ሲሆን እስከምታምኑ ድረስ በእኛና በእናንተ መካከል ጠብና ጥላቻ ዘወትር ተገለጸ::» ባሉ ጊዜ (መልካም መከተል አለቻችሁ)::" (ሙምተሂና ፡ 4)

ጥያቄ - 85፦ ከሀዲያንን በበአላቸው ጊዜ "እንኳን አደረሳችሁ" ማለት ለምሳሌ በክሪስ ማስ (ገና በዓል) ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 85፦ ሸይኽ ሙሀመድ ብን ዑሰይሚን - ረሂመሁሏህ - የሚከተለውን ተናግረዋል፦ "በክሪስማስ በአልም ይሁን በሌላው በአላቸው ከሀዲዎችን እንኳን አደረሳችሁ ማለት እርም ለመሆኑ የኡለሞች ስምምነት ነው።" ይህን ኢብን አልቀይም "አህካሙ አህሊ ዚማህ" በሚባለው ኪታቡ እንደጠቀሰው።" ፈታዋ ኢብን ዑሰይሚን (3/44)

ጥያቄ - 86፦ የቢድዓን ትርጉም ተናገር፤

መልስ - 86፦ የአላህ መልክተኛም ይሁን ሶሃቦች ባልነበሩበት አይነት አላህን መገዛት ማለት ነው።

ጥያቄ - 87፦ በዲን ውስጥ ቢድዓ ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 87፦ ቢድዓ እርም ነው። በጣም ብርቱ ከሆኑት ወንጀሎች ነው።

የአላህ መልክተኛ የሚከተለውን ተናግረዋል፦

"ከንግግሩ ሁሉ በላጭ የአላህ ኪታብ ነው። ከመመሪያው ሁሉ በላጭ የሙሐመድ መመሪያ ነው። ከነገሮች ሁሉ ክፉ ፈጠራዎቿ ናቸው። ማንኛውም (የዲን) ፈጠራ ጥመት ነው" (ሐዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል)

ጥያቄ - 88፦ በኢስላም ውሥጥ መልካም ቢድዓ ይኖራልን?

መልስ - 88፦ በኢስላም ውስጥ መልካም ፈጠራ የሚባል የለም።

የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“ማንኛውም ፈጠራ ጥመት ነው” (ሐዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል)

ጥያቄ - 89፦ በቢድዓ ባለቤቶች ላይ ሊኖር የሚገባው አቋም ምንድን ነው?

መልስ - 89፦ ግዴታው ከቢድዓ ባለቤቶች መጠንቀቅ፣ ከእነርሱም ማስጠንቀቅ፣ ከእነርሱ ጋር መቀማመጥን እንዲሁም መጽሐፋቸውን ከመመልከት መቆጠብ ነው።

ኢብን ዐባስ የሚከተለውን ተናግረዋል፦ “የዝንባሌ ባለቤትን አትቀማመጥ፤ ከእነርሱ ጋር መቀማመጥ ልቦችን ያሳምማል።” (አልኢባና (2/438))

ኢማም አልበገውይ የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“የቢድዓ ባለቤቶችን ጠላት በማድረግ እና በመራቅ ላይ የሶሃቦች፣ የታቢዒዮች የእነርሱም ተከታዮች የሱና ዓሊሞች ሁሉ ስምምነታቸው አንድ መሆኑ አልፏል።” (ሸርህ ሱና (1/127))

ጥያቄ - 90፦ ሶላትን መተው ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 90፦ ሶላትን መተው ክህደት ነው፡፡ ማስረጃው ጃቢር ያስተላለፈው የረሱል (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሐዲስ ነው

“በሰውየውና በሺርክ ወይም በክህደት መካከል ያለው ግርዶሽ ሶላትን መተው ነው፡፡” (ሐዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል)

ጥያቄ - 91፦ ያለአግባብ ሙስሊምን ማክፈር (ከሐዲ ማለት) ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ - 91፦ ያላግባብ ሙስሊምን ማክፈር እርም ነው፡፡ ከወንጀሎች ሁሉ በጣም ብርቱው ነው፡፡

የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“ማንኛውም ሰው ለወንድሙ “አንተ ካፊር (ከሐዲ)” ያለ ከሁለት አንዱ በእርሷ ይመለስበታል፡፡ እርሱ እንዳለው ከሆነ (የተባለው ሰው ይከፍራል)፡፡ ካልሆነ ግን (ክህደቷ) በእርሱ ላይ (በተናጋሪው ላይ) ትመለሳለች፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ጥያቄ - 92፦ የረሱልን ሶሃቦች አስመልክቶ የሙስሊም ግዴታው ምንድን ነው?

መልስ - 92፦ ግዴታው እነርሱን መውደድ ነው፡፡

ከነብያቶች እና ከመልክተኞች በኋላ ከሰዎች ሁሉ በላጭ ናቸው ብሎ ማመን:: በመልካም ማውሳት እንጅ እነርሱን አስመልክቶ (ከመጥፎ) ንግግር መቆጠብ:: ከሰሃቦች መካከል አንዱን መሳደብ እርም ነው::

የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“ሶሃቦቸን አትሳደቡ:: ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ ከእናንተ መካከል አንዱ የኡሁድ ተራራ ያክል ወርቅ ቢለግስ ከእነርሱ አንድ እፍኝ ወይም ግማሹን ከለገሰው ጋር አይስተካከልም::” (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ጥያቄ - 93፦ ሶሃቦች በላጭ ለመሆናቸው ምንድን ነው ማስረጃው?

መልስ - 93፦ ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

﴿ وَالسَّابِقُونَ الْأَوَّلُونَ مِنَ الْمُهَاجِرِينَ وَالْأَنْصَارِ وَالَّذِينَ اتَّبَعُوهُمْ بِإِحْسَانٍ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُوا عَنْهُ وَأَعَدَّ لَهُمْ جَنَّاتٍ تَجْرِي تَحْتَهَا الْأَنْهَارُ خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا ۚ ذَٰلِكَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ﴾

“ከስደተኞችና ከረዳቶችም ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎች እነዚያም በበጎ ስራ የተከተሏቸው አላህ ከእነርሱ ወዷል ከእርሱም ወደዋል:: በስሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ጀነቶች በውስጣቸው ዘላለም

ነዋሪዎች ሲሆኑ ለእነርሱ አዘጋጅቶላቸዋል። ይህ ታላቅ እድል ነው።"(ተውባ፡ 100)

ጥያቄ - 94፦ ከሶሃቦች በላጩ ማን ነው?

መልስ - 94፦ ከሶሃቦች በላጩ አራቱ ኹለፋዎች ናቸው። እነርሱም አቡበክር ሲዲቅ፣ ከዚያም ኡመር ብን አልኸጧብ፣ ከዚያም ኡስማን ብን አፋን፣ ከዚያም አልይ ብን አቢጧሊብ ናቸው። ከዚያም አስሩ በጀነት የተበሰረላቸው ናቸው።

ጥያቄ - 95፦ የስልጣን ባለቤት ሲባል የታሰቡት እነማን ናቸው?

መልስ - 95፦ የታሰቡት የሙስሊም ባለስልጣኖች ናቸው።

ጥያቄ - 96፦ የስልጣን ባለቤቶችን አስመልክቶ በሙስሊሞች ላይ ያለው ግዴታ ምንድን ነው?

መልስ - 96፦ የአላህን ህግ ከሚጻረሩ ነገሮች ውጭ መሪዎችን መስማት እና መታዘዝ ግዴታ ነው። እነርሱን (በስርዓት) መምከር፣ ለእነርሱም ዱዓ ማድረግ፣ እነርሱን በየመድረኩ በየስብሰባው አለማጥላላት - ምክንያቱም ፊትና ይቀሰቅሳልና።

ጥያቄ - 97፦ በዚህ ላይ ማስረጃው ምንድን ነው?

መልስ - 97፦ ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي الْأَمْرِ مِنْكُمْ

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ መልክተኛውንና የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ።” (ኒሳእ ፡ 59)

ሌላው ማስረጃ የአላህ መልክተኛ ንግግር ነው፦

“ዲን ማለት መመካከር ነው። የአላህ መልክተኛ ሆይ ስለምንድን ነው (የምንመካከረው)። ስለአላህ ፣ ስለ መጽሐፉ፣ ስለ መልክተኛው፣ ስለ ሙስሊም መሪዎች እና ስለህዝቡ ነው።” (ሐዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል)

ጥያቄ - 98፦ የሙስሊም ባለስልጣኖችን እንዴት ነው የምንመክረው?

መልስ - 98፦ የምንመክረው በሚስጢር መሆን አለበት።

የአላህ መልክተኛ የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“ባለስልጣንን መምከር የፈለገ ሰው በይፋ ግልጽ አያድርገው። ነገር ግን እጁን ይዞ ገለል አድርጎ ይምከረው። ከእርሱ ከተቀበለው መልካም። ካለበለዚያ በእርሱ ላይ ያለውን ሀቅ ተወጣ።” (አህመድና ሌሎች ዘግበውታል። አልባኒ እንዲሁም ኢብን ባዝ ሶሂህ (ትክክለኛ ሐዲስ ነው) ብለውታል።)

ጥያቄ - 99፦ ፊትና ሲከሰት የሙስሊም ግዴታው ምንድን ነው? ከመረጃ ጋር

መልስ - 99፦ ግዴታው ከፈተና መራቅ፤ የሙስሊምን ጀማዓ እና ኢማማቸውን አጥብቆ መያዝ፤ የጥልቅ እውቀት ባለቤቶችን መጠየቅ ነው።

ማስረጃው የአላህ ቃል ነው፦

﴿ وَإِذَا جَاءَهُمْ أَمْرٌ مِنَ الْأَمْنِ أَوِ الْخَوْفِ أَذَاعُوا بِهِ ۖ وَلَوْ رَدُّوهُ إِلَى الرَّسُولِ وَإِلَىٰ أُولِي الْأَمْرِ مِنْهُمْ لَعَلِمَهُ الَّذِينَ يَسْتَنْبِطُونَهُ مِنْهُمْ ۗ وَلَوْلَا فَضْلُ اللَّهِ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَتُهُ لَاتَّبَعْتُمُ الشَّيْطَانَ إِلَّا قَلِيلًا ﴾

“ከጸጥታ ወይም ከፍርሀት አንዳች (ወሬ) በመጣላቸውም ጊዜ እርሱን ያጋንናሉ። ወደመልክተኛውና ከእነርሱ ወደትእዛዙ ባለቤቶች (ወደአዋቂዎቹ) በመለሱት ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ (ነገሩን) የሚያውጣጡት ባወቁት ነበር። በእናንተም ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ ከጥቂቶች በስተቀር ሰይጣንን በተከተላችሁ ነበር።” (ኒሳእ፡ 83)

ጥያቄ - 100፦ አህለሱና ወልጀማዓ እነማን ናቸው?

መልስ - 100፦ እነርሱ የነብዩን እንዲሁም የሶሃቦችን ሱና አጥብቀው የሚይዙ፤ በእምነት፣ በንግግር በተግባር የእነርሱን መንገድ የተጓዙና የተከተሉ ናቸው።

وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وصحبه أجمعين